# በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ላኪዎች በግብአት ላይ የከፈሉት ታክስ በተፋጠነ አኳኋን እንዲመለስ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 26/2001

## 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በተሻሻለው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 543/1999 አንቀጽ 22 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ላኪዎች የከፈሉት ታክስ በተፋጠነ አኳኋን እንዲመለስ ለማድረግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 26/2001» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ላኪዎች በአገር ውስጥ በሚፈፅሙት ግዥ ላይ የከፈሉት ታክስ በተፋጠነ አኳኋን ተመላሽ እንዲሆን በማድረግ የአገር ውስጥ ምርቶችን መጠቀምን ማበረታታት ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ የሚሆነው በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ላኪዎች ለምርታቸው በግብአትነት የሚጠቀሙበትን ጥሬ ዕቃ ከአገር ውስጥ በሚገዙበት ጊዜ ለከፈሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሣይዝ ታክስ ይሆናል፡፡

2. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 26/2000 በተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ተመላሽ የተደረገላቸውን ሂሳብ በሚያወራርዱበት ጊዜ ይሆናል።

## 5. የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚዎች

በዚህ መመሪያ የተዘረጋው የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት:-

1. በወጪ ንግድ ሥራ ላይ በመሠማራት ለአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ የሚገኙ እና ታክስ የመክፈል ግዴታቸውን የተወጡ፣

2. በንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር እና/ወይም በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መመዘኛ መሠረት ተገምግመው በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ የተደረገ፣

ላኪዎች ናቸው።

## 6. የተፋጠነ ሥርዓት

1. የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚዎች ለዚሁ ዓላማ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡት ምርት ማምረቻ እንዲውል በአገር ውስጥ በፈፀሙት የግብአት ግዥ ላይ የከፈሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሣይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ጥያቄያቸውን በየወሩ ለባለሥልጣኑ ለማቅረብ ይችላሉ።

2. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አመልካቹ በሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የኤክሣይዝ ታክስ የተከፈለበትን ማስረጃ ትክክለኛነት በማጣራት ጥያቄው በቀረበ በ7 ቀን ጊዜ ውስጥ የተከፈለውን የታክስ ሂሳብ ለላኪው ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## 7. ሪፖርት የማድረግ ግዴታ

የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ላኪዎች ከአገር ውስጥ በገዙት ግብአት የተመረተው ምርት ወደውጭ መላኩን የሚያረጋግጥ በተሻሻለው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር **543/1999** አንቀጽ **6--8** በተደነገገው መሠረት የተዘጋጀ ሪፖርት ከአስፈላጊው መረጃ ጋር በማያያዝ የከፈሉት ታክስ ተመላሽ ከተደረገላቸው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 8. የተከፈለውን ሂሳብ ተመላሽ ስለማድረግ

የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ላኪዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 በተመለከተው መሠረት የተሟላ ሪፖርት ያላቀረቡ ወይም የቀረበው ሪፖርት በአገር ውስጥ በፈፀሙት የግብአት ግዥ ተጠቅመው ያመረቱት ምርት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለውጭ ገበያ መቅረቡን የማያረጋግጥ ከሆነ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ለውጭ ገበያ ባልዋለው መጠን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2) መሠረት ተመላሽ የተደረገውን ሂሳብ እንዲሁም በዚሁ ሂሳብ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ወለድ (በማበደሪያ ወለድ ተመን መሠረት) አስልቶ እንዲከፍሉ ያደርጋል፡፡

## 9. አዲት ስለማድረግ

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ላኪዎችን የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ እና ከንግድ ሥራው እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በመመርመር የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

## 0. የመብቱ መቋረጥ

የተፋጠነ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ላኪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 እና 8 የተመለከተውን ግዴታውን ካልተወጣ በመብቱ ተጠቃሚ የመሆን መብቱ ይቋረጣል፡፡

## 01. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ነሐሴ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር*